02


1ኛ ዓመት ቁጥር 16
1st Year No. 16



ባሕር ዳር ጥቅምት 27ቀን 1989
Bahir Dar 5th November 1996


በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ
# ZIKRE HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE
IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA


| | | |
|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር 1.00 | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባቂነት የወጣ | የፖ.ሣ.ቁ. 312 P. O. BOX |



ማ ው ጫ

አዋጅ ቁጥር 16/1989 ዓ.ም. በአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት ይዞታ ሽግሽግን ለማካሄድ የወጣ አዋጅ ገጽ 11

CONTENTS

Proclamation No 16,1996
A Proclamation to Provide for the reallotement of the Possession of Rural land in the Amhara National Region
Page 11


## አዋጅ ቁጥር 16/1989 ዓ.ም. በአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት ይዞታ ሽግሽግን ለማካሄድ የወጣ አዋጅ

ለገጠሩ አርሶ አደር የመሬት ጥያቄ፣የኢኮኖሚው መሠረት ብቻ ስለሆነ ሳይሆን ሕገ መንግስታዊ መብቱም በመሆኑ፣

ባለፈው ሥርዓት ምንም እንኳ መሬት የህዝብ ሀብት ሆኗል ተብሎ ቢታወጅም በአብዛኛው የሃገራችን ክፍል የገጠሩ መሬት በጥቂት የሥርዓቱ አቀንቃኝ በነበሩ ቢሮክራቶች እና የገበሬ ማህበር ተመራጮች በመያዙ ምክንያት ሰፊ የይዞታ አለመመጣጠን የሚታይ ከመሆኑም በላይ ሰፊው አርሶ አደርም በድህነት አረንቋ ውስጥ እንደዘፈቅ በመደረጉ፣

ይህንኑ አሰብዓዊ የሆነ ሞቆና ለማስወገድ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙንም ለማስከበር ሰፊው አርሶ አደር በኢህአዴግ ጥላስር ተሰባስቦ ባካሄደው የሞት ሽረት ፍልሚያ ጨቋኙን የደርግ ሥርዓት ገርስሶ በመጣልና በመረጣቸው

## Proclamation No 16,1996
## Proclamation to Provide for the reallotement of the Possession of Rural land in the Amhara National Region

Where as, the question of land for the peasantry is not only the basis for his economic life but also constitution right, too,

Where as, during the past regime ,though, land was proclaimed to be a public property, the rural land in many parts of the country has been grabbed by few bureaucrats and elects of agricultural cooperatives who have been proponents of the regime; and this resulted in the wide and unbalanced possession of rural land which inturn, subjected the broad peasant to languish in an abject poverty,

Where as in order do away with this inhuman operassion and to maintain its economic benefit, the broad peasant had organized himself under the umbrella of EPRDF and waged a life to death struggle



145

ተወካዬቹ አማካይነት ባፀደቀው ሕገ-መንግስት የገጠር መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት የሕዝብና የመንግስት መሆኑ መሬትንም በእኩልነትና በነፃነት የማግኘት መብቱን ያረጋገጠ በመሆኑ፤

በክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ ከ1983 ዓ.ም. በፊት ከደርግ አገዛዝ ነፃ በወጡት አካባቢዎች ፍትሃዊ የሆነ የመሬት ክፍፍል ፖሊሲ ተነድፎ መሬት አልባ የነበሩት አርሶ አደሮች የመሬት ይዞታ ባለመብት የሆኑበት ሁኔታ ሲኖር፤ከ1983 ዓ.ም ወደህ ነፃ በወጡ አካባቢዎች ግን የመሬት ክፍፍል ባለመከናወኑ፤ አርሶ አደሩ በተደጋጋሚ የሚያነሣው አንገብጋቢና ምላሽ ማግኘት ያለበት ጥያቄ እየሆነ ከመምጣቱም በላይ፤ በክልሉ ውስጥም የተከሰቱትን ሁለት ዓይነት ስሪቶች አስወግዶ ፍትሀዊ የሆነ የመሬት ይዞታ ሥርዓት እንዲሰፍን ማድረግ በማስፈለጉ፤

የክልሉ መንግስት ቡተነደፈው የ5 ዓመት የልማት የሠላምና የዲሞክራሲ መርሀ ግብር መሠረት፤በአንድ በኩል የአርሶ አደሩን መሬት በይዞታ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብት እውን ለማድረግ፤በሌላ በኩል ደግሞ ከተዘፈቀበት የድህነት አረንቋ ውስጥ አውጥቶ ዙርያ መለስ ለሆነ ፈጣን የኢኮኖሚ ለውጥ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ በቅድሚያ የተባባውን የመሬት ይዞታ ሥሪት አስወግዶ ፍትሀዊ የሆነ የመሬት ሽግሽግ ማካሄድ ተገቢ በመሆኑ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ም/ቤት በክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3(1) መሠረት የሚከተለውን አውጆአል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት ይዞታን ለማሻሻያ የወጣ አዋጅ ቁጥር 16/1989 ዓ.ም. ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ

1. "ክልል" ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልል ህገ-መንግሥት አንቀጽ2 መሠረት የተቋቋመውን የአማራ ብሔራዊ ክልል ማለት ነው፤
2."የገጠር መሬት" ማለት ከከተማ ክልል ውጭ ያለ ማንኛውም መሬት ነው፤
3."የመሬት ይዞታ መብት" ማለት መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የሕዝብና የመንግስት ሀብት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አርሶ አደር ሊጠቀምበት በነፃ ያገኘውን መሬት ለእርሻ ለግጦሽ እና ለመሳሰሉት ተግባራት የማዋል የማከራየት እንዲሁም በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ቋሚ ንብረት የመገንባት የጎላውን

and over throw the oppressive regime of derg which inturm enabled him to ratify a constitution through his elected representatives that in effect assured the owner ship of the rural land and natural resources to the public and to the state, and alsogaratee the right to be allotted land equally and freely.

Where as, in the objective situation of our region, those areas that were freed from the derg regime before 1991, a fair land distribution policy was designed in which land less peasants have been given the right to possess land, while in areas that were freed from the derg regime after 1991, since no distribution of land has been carried out, for the peasantry land has become a burning and repeatedly raised question that needs an immediate reply, besides it has become necessary to do away the phenomena of two system of land possession in the region by replacing the same with a fair system of land possession,

Where as, according to the five years development, peace and democracy program designed by the regional Government; in order to ensure the constitutional right of the peasantry to get land in possession on the one hand and to deliver him from languishing in an abject poverty on the other , and also to make him beneficiary of the all running rapid economic change , primarily it is appropriate to do away with the unbalanced system of land possession and there by carry out fair reallotment of the same,

Now there fore in accordance with Article 49 sub article 3(1) of the constitution of the council of the Amhara National Regional state here by proclaimed as follows;

## PART ONE
## GENERAL

**1. SHORT TITTLE**

This proclamation, may be cited as The Amhara National Region reallotment of rural land possession Proclamation No 16/1996

**2. DEFINITION**

Unless the context requires other wise:

1."Region" means the Amhara National Region established as refered to in Article 2 of the constitution of the amhara National Region.
2."Rural Land" means any land located outside the boundary of urban areas.
3."The Right of possession of Land" means with out prejudice to the principle that land is a public and governmental property which is not subjected to sell , or barter; encompasses such right of the peasants who have got land freely to utilize it for farming , grazing and other purposes; and also rent it a well as building permanent properties employing his labour or

ንብረት የመሸጥ የመለወጥ የማውረስ መብቱን የሚያጠቃልል ነው፤

4."የመሬት ይዞታ ሽግሽግ" ማለት በገጠር የቀበሌ ክልል ውስጥ የሚገኙትን የእርሻና የግጦሽ መሬቶች በሕዝብ ውሳኔ ፍትሀዊ በሆነና በተመጣጠነ መንገድ የቀበሌ ነዋሪ ለሆኑ አርሶ አደሮች በእርሻ መሬትነት የሚከፋፈልበትን እና ለቀበሌ ሕዝብ የጋራ ጥቅም እንደውሉ የሚደረግበት አግባብ ነው፡፡

5. "ቤተሰብ" ማለት በአንድ ጣሪያ ሥር የሚኖሩና እንደሁኔታው በወንድ ወይም በሴት ኃላፊነት የሚተዳደሩ፤ የሥጋና የጋብቻ ዝምድና ያላቸውን ወላጆች፤ልጆች እና የጉዲፈቻ ልጆችን የሚያጠቃልል ማኅበራዊ ተቋም ነው፡፡

6."የቤተሰብና የመሬት ይዞታ አጣሪ ኮሚቴ" ማለት በእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ ክልል ነዋሪ ሕዝብ የሚመረጥና በቀበሌው ክልል ውስጥ የሚገኙትን ቤተሰቦች ብዛት ያላቸውን የመሬት ይዞታ መጠን በማጣራት ምዝገባ የሚያካሂድ አካል ነው፤

7."ደልዳይ ኮሚቴ" ማለት በእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ ክልል በነዋሪው ሕዝብ የሚመረጥና የመሬት ይዞታ ሽግሽግና ድልደላ የሚያከናውን አካል ነው፤

8."ቋሚ አትክልት" ማለት አርሶ አደሮች በይዞታቸው ላይ የሚተክሏቸው ከአንድ አመት በላይ ለሆነ ጊዜ የሚቆዩና በየጊዜው ጥቅም የሚሰጡ ተክሎች ማለት ነው፡፡

3.የተፈፃሚነት ወሰን

1.ይህ አዋጅ ተፈፃሚነት በአማራ ብሔራዊ ክልል፤በከተማነት ከተከለሉ አካባቢዎች ውጭ፤ በእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ ክልል ውስጥ በሚገኙ የእርሻና የግጠሽ መሬቶች ላይ ይሆናል፡፡

2.ከ1983 ዓ.ም. በፊት ከደርግ አገዛዝ ነፃ በወጡ የክልሉ አካባቢዎች የመሬት ክፍፍሉ የተከናወነ በመሆኑ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በእነዚህ አካባቢዎች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

3.በ1983 ዓ.ም. ከደረግ አገዛዝ ነፃ በወጡት የክልሉ አካባቢዎች የመሬት ክፍፍሉ ባለመከናወኑ በነዚህ አካባቢዎች የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

4.በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት በእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ ክልል ውስጥ የሚከናወነው የመሬት ሽግሽግ በቀበሌው ክልል ውስጥ በሚገኙ የእርሻና የግጦሽ መሬቶች ላይ ይሆናል፡፡

4. የሞፈር ዘመት የመሬት ይዞታ ስለመከልከሉ

ከእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ ክልል ውጭ የሚከናወን ማንኛውም ዓይነት የሞፈር ዘመት የመሬት ይዞታ በዚህ አዋጅ የተከለከለ ነው፡፡

money ; sell, barter or inherit the same.

4." Reallotment of Land possession" means a mechanism where by farm and grazing lands found in the rural kebeles are to be distributed the peasant inhabitants of the respective Kebeles,in order to be used as a farm land and also the mutuat benefit of the public in the concerned kebekes based on the decision of the same and in a fair and balanced manner

5."Family" means the social institution run under the responsibility of the male or the female, encompassing the parent's children and adopted children who live under the same roof having the relation ship of affinity and consanguinity.

6."Family and Land possession verifying committee" means a body nominated by the in habitants of each rural kebeles to carry out the work of registration after verifying the number of families to be found in the respective kebeles and the size of the land under their possession.

7."Alloting committee" means a body nominated by the inhabitants of each rural kebele to carry out the work of reallotting and distributing land in each respective kebele.

8."Perennial plant" meaus plants which are cultivated by peasants in their respective possessions and stay for more than a year and bear fruits periodically.

3. Scope of application

1. The scope of application of this proclamation shall be in the amhara national region up on every farming and grazing lands located in each respective rural kebeles; out side the boundary of urban areas.

2.The provisions of this proclamation shall not apply to the areas freed from the derg regine before 1991 since the redistribution of land has already been accomplished.

3. The provisions of this proclamation shall apply to the areas freed from the derg regime after 1991, since the redistribution of land has not yet been accomplished there.

4.with out prejudice to the sub Article 1 of the provision of this Article the reallotment to be carried in each rural kebeles, in accordance with this proclamation, shall apply up on farms and grazing lands located in each respective kebeles.

4. The prohibition of the possession of Land out side the boun dary of the Kebeles.

Any act of possession of land practiced out side the boundary of each respective rural kebeles is prohibited by this proclamation.

## ክፍል ሁለት
## ስለመሬት ይዞታና የቤተሰብ ብዛት ምዝገባ እና የመሬት ሽግሽግ አጠቃላይ አፈፃፀም

**5.የመሬት ይዞታን ስለማጣራት**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 ድንጋጌ መሠረት የሚቋቋመው አጣሪ ኮሚቴ፣

1.በቀበሌው ውስጥ በሚኖሩት ነዋሪዎች ይዞታ ሥር የሚገኘውን የመሬት ልክ አጣርቶ ይመዘግባል፣

2.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አስፈላጊውን ምዝገባና የማጣራት ተግባር ካከናወነ በኃላ የደረሰበትን ውጤት ለቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ አቅርቦ ያወያያል፣

3.የቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ በቀረበው ዘገባ ላይ ተወያይቶ ከተገቢው ማሻሻያ ጋር ካፀደቀው በኃላ ይህንኑ የህዝብ ውሳኔ ሰነድ ለቀጣዩ አፈፃፀም ለሚቋቋመው የይዳዳይ ኮሚቴ በሕዝብ ፊት ያስረክባል።

**6.የቤተሰብ ብዛትን ስለማጣራት**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 ድንጋጌ መሰረት የሚቋቋመው አጣሪ ኮሚቴ፣

1.በቀበሌው ክልል ውስጥ የሚኖሩትን ቤተሰቦች እና በእያንዳንዱ ቤተሰብ ሥር የሚኖሩትን አባላት ብዛት አጣርቶ ይመዘግባል፣

2.በቀበሌው ውስጥ ሆነው በተለያየ ምክንያት መሬት በይዞታ ያላገኙትን የቀበሌው ነዋሪዎች እና በአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 10 መሠረት በቋሚነት በቀበሌው ውስጥ ለመኖር የወሰኑትን አጣርቶ ይመዘግባል፣

3.በዚህ አንቀጽ ን/አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት አስፈላጊውን ምዝገባና ማጣራት ካከናወነ በኃላ የደረሰበትን ውጤት ለቀበሌው ነዋሪ ህዝብ አቅርቦ ያወያያል፣

4.የቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ በቀረበው ዘገባ ላይ ተወያይቶ ከተገቢው ማሻሻያ ጋር ካፀደቀው በኃላ ይህንኑ የሕዝብ ውሳኔ ሰነድ ለቀጣዩ አፈፃፀም ለሚቋቋመው የይዳዳይ ኮሚቴ በሕዝብ ፊት ያስረክባል።

**7. የመሬት ሽግሽግ ስለማከናወን**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 ድንጋጌ መሠረት የሚቋቋመው የመሬት ይዞታ ይዳዳይ ኮሚቴ፣

1.ከአጣሪ ኮሚቴ የተረከበውን የነዋሪ ሕዝብ ብዛትና የሚከፋፈለውን የመሬት ይዞታ መጠን በማመዛዘን ለእያንዳንዱ ቤተሰብ የሚደርሰውን የመሬት ይዞታ ይወስናል፣

2.መሬት የሚቀነስባቸውንና መሬት ሊያገኙ የሚገባቸውን ሰዎች ዝርዝርና የሚሸጋሸገውን የመሬት መጠን በተመለከተ ያዘጋጀውን መነሻ ሀሳብ ለቀበሌው ሕዝብ አቅርቦ እንዲወያይበት ያደርጋል፣

## PART TWO
## The General Implementation of Land possession and Family size registration and Reallotment of Land.

**5.Verifying Land Possession**

The verifying committee established in accordance with the provision of article 14 of this proclamation shall:

1.Register, after verifying the size of the land under the possession of the inhabitants of the kebele.

2. present the achieved result to the inhabitants of the kebele and cause a discussion there of after accomplishing the necessary registration and verification persuant to sub article 1 of this article

3. submit the instrument that holds the public decision to the reallotment committee to be established for the implementation of the same before the public, after the inhabitants of the kabele hold discussion upon the submitted report and ratify it with the necessary recommendation

**6.Verifying family size**

The verifying committee established inaccordance with the provision of article 15 of this proclamation shall:

1. Register, after verifying the size of the families of the respective kebele and the number of the members under each family

2. Register, after verifying those in habitants of the kebele who did not possess land owing to different reason and those who have decide to live permanently in the kebele persuant to sub article 10 of article 11.

3. Present the achieved result to the inhabitants of the kebele and hold discussion, after accomplishing the necessary registration and verification, inaccordance with subarticle 1 and 2 of this article.

4. Submit the instrument that holds the public decision to the reallotment committee, to be established for the implementation of the same before the public, after the inhabitants of the kebele hold discussion upon the submitted report and ratify it with the necessary recommendation.

7. **Implementing the reallotment of land**

The land possession reallotting committee established in accordance with the provision of article 18 of this proclamation shall:

1. Decide the size of land possession to be allotted to each family, by balancing between the size of land to be allotted and the Number of in habitants as received from the verifying committee.

2. conduct a discussion by presenting its proposal to the inhabitants of the respective kebele which it prepares concerning the list of person whose land possession is to be reduced and to whom land has to be allotted, and as well as the size of land subjected to allotment.

3.በዚህ አንቀጽ 3/አንቀጽ 1 እና 2 ሥር የተደነገጉትን ተግባራት ከፈጸመ በኃላ የሚሸጋሸገውን መሬት ለእጣ ያዘጋጃል፣
4.በትርፍነት የተመዘገበውን መሬት በቀበሌው ውስጥ መሬት እንዲያገኙ ለተወሰነላቸው ግለሰቦች በዕጣ ያከፋፍላል፣
5.ያመሬት ድልድሉን ሲያከናውን የለሙና ቋሚ አትክልት ያለባቸውን ቦታዎች በተመለከተ በተቻለ መጠን, መሬቶቹን በሕጋዊ መንገድ ይዘው በጉልበታቸው ወይም በገንዘባቸው አትክልቱን ባለሙ ነባር ባለይዞታዎች ሥር የሚፀኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
6.ያዕጣው አወጣጥ ሥርዓት የሚፈፀመው የደልዳይ ኮሚቴው አባላት፣ ታዛቢ ሽማግሌዎች፣ የቀበሌው መስተዳድር አባላት እና ዕጣ የሚወጣላቸው አርሶ አደሮች በተገኙበት በሕዝብ ፊት ይሆናል፣
7.ያድልድል ተግባሩን ሲያከናውን በነባር ባለይዞታዎች እና በአዲስ ባለይዞታዎች መካከል በውሃ ገብ የአትክልት መሬቶች እንደሁም ከፍተኛና ዝቅተኛ ለምነት ባላቸው መሬት ላይ ፍትሃዊ የሆነ የማመጣጠን ተግባር የመፈፀም ኃላፊነት አለበት፣

8. <u>ስለ ካሣ እና አሳባ አከፋፈል</u>

1.ባለፈው ሥርዓት የነበራቸውን ስልጣን መከታ በማድረግ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የአርሶ አደሩን መሬት ነጥቀው ያለሙ ግለሰቦች የሚያቀርቡት የካሣ እና የአሳባ ጥያቄ በዚህ አዋጅ ተቀባይነት አይኖረውም፣
2.በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀደም ሲል መሬት በሕጋዊ መንገድ ይዘው ያለሙ አርሶ አደሮች በዚህ አዋጅ መሰረት ቦተፈፀመ ሽግሽግ ምክንያት በጉልበታቸውና በገንዘባቸው ያለሙትን የቀድሞ ይዞታቸውን ቢያጡ መሬቱን በሽግሽግ ከተረከበው አዲስ ባለይዞታ ተገቢውን ካሣ እና አሳባ ያገኛሉ፡፡
3.የካሣ እና አለባ አከፋፈል በአካባቢው ተመን በባህላዊ መንገድ የሚወሰን ሆኖ በገንዘብ፣ በዓይነት፣ ወይም በጉልበት የሚፈፀም ሊሆን ይችላል፣
4.የቀበሌው መስተዳድር የካሣ እና አለባ ክፍያን በተመለከተ የሚሰጠውን ውሳኔ የማስፈፀም ኃላፊነት ይኖረዋል፣ ዝርዝር አፈፃፀሙ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያ ይወሰናል፡፡

9. <u>ለሕዝብ የጋራ ጥቅም ስለሚውሉ መሬቶች</u>

በእያንዳንዱ የገጠር የቀበሌ ክልል ውስጥ ለሕዝብ የጋራ ጥቅም የተከለሉና የሚከለሉ፣ ለመኖርያ ቤት መሥርያ፣ ለግጦሽ፣ ለደን እና ለማኅበራዊ አገልግሎት የሚውሉ መሬቶችን አጠቃቀም በተመለከተ እንደ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በሕዝቡ ይወሰናል፡፡

3. Prepare the land to be allotted for a lot, after accomplishing the acts provided in sub article 1 and 2 of this article
4. Distribute the remained registered land by casting a lot to those persons who are allowed to get land in their respective kebeles.
5. Facilitate conditions, while carring out the reallotment of land in which lands which have been highly cultivated with pernerial plants may remain in the hands of their former possessors as much as possible, who have got the lands legally and cultivated them by employing their own Labour and money.
6. The procedures of casting a lot shall be executed before the public in the presence of the members of the reallotting committee elder observant, members of the kebele adiminstration and peasants who are entitled to the lot.
7. Have the responsibility of balancing in a fair manner between the former and the new possessors of the land while caring out the reallotment of the land of vegitation and water accessed ones and lands of high and law fertility rate.

**8. Payment of compensation and fructus**

1. The claims for compensasion and the fruit of land by those persons of the past regime who using their position has ilegally taken away the lands of the peasants and has been cultivating it, shall not be accepted under this proclamation.
2. With out prejudice to sub article 1 of this article, the peasants who formerly possessed the Land in a legal way and had been cultivating by employing their labour and money owing to the reallotment of land carried under this proclamation; if thier land is taken away they shall get appropriate compensation and payment of the fruit of land from the new possessors who received it due to the reallotment
3. Payment of compensation and the fruit of land, being determined in traditional way according to the local market price; may be effected in cash ,kind or labour.
4. The Kebele administration shall have the responsibility to execute the decision rendered concerning the payment of compensation and fruit of land; details of the implementation shall be determined by regulation or directives persuant to this proclamation.

9. **Lands to be used for the mutual benefit of the public**.

Concerning the use of lands which has been staked or to be staked out for the mutual benefit of the public, and lands to be used for construction of doweling houses, graces, fores try and other social services in each rural Kebele shall be determined by the public in accordance with the objective situation of the respective localities.

## ክፍል ሦስት
## የገጠር መሬት በይዞታ ለመያዝ ስለተፈቀደላቸው ሰዎች

### 10. ስለ ነባርና አዲስ ባለይዞታዎች መብት

ማናቸውም ቀደም ሲል የገጠር መሬት ይዘው የነበሩ እና ቀደም ሲል መሬት ያልነበራቸው በዚህ አዋጅ ድንጋጌ መሠረት መሬት ለመያዝ የተፈቀደላቸው የገጠር ነዋሪዎች በሙሉ ያታ ሳይለይ መሬት በይዞታ የመያዝ መብት አላቸው።

### 11. የገጠር መሬት ለመያዝ የተፈቀደላቸው አዲስ ባለ ይዞታዎች

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ድንጋጌ መሠረት በሚኖሩበት የገጠር ቀበሌ ክልል ውስጥ መሬት ለመያዝ መብት የሚኖራቸው ግለሰቦች የሚከተሉት ናቸው

1.ቤተሰብ የሚያስተዳድሩ የቤተሰብ ኃላፊዎች
2.በ1988 ዓ.ም.እና ከዚያ በፊት ጋብቻ መሥርተው ጎጆ የወጡ ባለትዳሮች
3.ከልጆቻቸው ወይም ከጧሪዎቻቸው ጋር ለመኖር የወሰኑ ተጧሪዎች
4.ቀደም ሲል ለአካለ መጠን ደርሰው ጎጆ ወጠው የነበሩ ወይም በሐብት እጦት ምክንያት ጎጆ ያልወጡ በሚኖሩበት የገጠር ክልል በሰው ቤት በሠራተኝነት ተቀጥረው የሚተዳደሩ

5. ኑሮአቸው በገጠር ክልል ሆኖ ጥጥ፣ በመፍተል፣ አረቄ በማውጣት፣ ጠላ በመጥመቅ፣ ወዘተ የሚተዳደሩ ሴቶች
6.መኖሪያቸው በገጠር የሆነና ኑሮአቸው በእርሻ ሥራ ላይ የተመሠረተ አነስተኛ ነጋዴዎች
7.ኑሮአቸው በዋነኝነት በእርሻ ላይ የተመሠረተ የከተማ ነዋሪ የሆኑ
8.መኖሪያቸው በገጠር የሆነና ቀደም ሲል መሬት ይዘው ሲተዳደሩ የነበሩ ጡረተኞች

9.መሠረታዊ መተዳደሪያቸው የእርሻ ሥራ ሆኖ አሁን ግን በምርጫ ምክንያት ከተማ ውስጥ በኃላፊነት ቦታ የተመደቡ የሕዝብ ተመራጮች
10. ከሌላ የገጠር አካባቢ አሁን ወደ ሚኖሩበት የገጠር ቀበሌ መጥተው ከ5 ዓመት ላላነሰ ጊዜ በአካባቢው የቆዩ ለወደፊቱም በዚህ የገጠር ክልል ውስጥ በቋሚነት ለመኖር የወሰኑና ከነበሩበት የገጠር ክልል መሬት በስማቸው ያልነበራቸው ወይም ያልያዙ ለመሆናቸው ማስረጃ የሚያመጡ

11.በገጠር ከእርሻ ሥራ ሳይርቁ በአነስተኛ የእደ ጥበብ ሥራ ተሰማርተው የሚኖሩ

### 12. የገጠር መሬት በይዞታ ለመያዝ ስላልተፈቀደላቸው

አግባብ ያላቸው የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 10 እና 11 ድንጋጌዎች ሥር

## PART THREE
## Persons Allowed to Hold Rural Land in possession.

### 10. The Right of the former and New possessers

Those rural inhabitants who formally held rural lands in possession and those who do not hold but allowed to possess the same prsuant to this proclamation, shall have the right to hold land in possecession with out any sexual discrimination.

### 11. New holdes allowed to possess a rural Land.

In accordance with article 10 of this proclamation the following persons shall have the right to hold lands in their respective dwelling rural kebeles.

1. Heads, administering families.
2. Couples, who have married before 1996 and has been living together in their own house.
3. Pensioners who have decided to live together with their children or those who pentioned them.
4. Persons who have attended marriageable age earlier and have been married, or due to lack of money couldn't make marriage and have been working as servants in the house of others in their respective dwelling rural localities.
5. Women living in the rural locality and make money for living by spinning cotton, brewing tela and araky ...etc.
6. Small traders who are living in rural localities and their means of subsistence is based on Agriculture.
7. Town dowellers whose means of existence is mainly based on agriculture.
8. Pensioners who are the inhabitants of the living rural locality and has held land formerly for their living.
9. Public elects whose basic means of existence depends on agriculture, but now due to election has been assigned in town in responsible position.
10. Persons who came from another rural locality to their present dwelling rural kebele and has been staying for not less than five years and have decided to reside permanently in the future and who can produce a document from their former dwelling rural locality which testifies that they have no land in their name or had not hold one.
11. Persons who with out being separated from agricultural activities has been engaged in small scale hand craft, in rural locality.

### 12. Persons Prohibited to hold Rural Land in Possession.

With out prejudice to the provision of other relevant laws, it is prohibited to hold arural land in possession except the in habitants of the rural

ከተዘረዘሩት የገጠር ነዋሪዎች በስተቀር የገጠርን መሬት በይዞታ መያዝ አይፈቀድም።።

## ክፍል አራት
## አዋጁን ለማስፈፀም ስለሚቋቋሙ ኮሚቴዎች

13. የመሬት ይዞታ እና የቤተሰብ ብዛት አጣሪ እና ደልዳይ ኮሚቴ ስለማቋቋም

ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም በእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ ክልል ውስጥ የቤተሰብና የመሬት ይዞታ አጣሪ እና ደልዳይ ኮሚቴዎች ይቋቋማሉ።።

14. የመሬት ይዞታ አጣሪ ኮሚቴ አወቃቀር

በእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ ክልል ውስጥ በነዋሪው ሕዝብ የሚመረጥ የመሬት ይዞታ አጣሪ ኮሚቴ ይቋቋማል
በተጨማሪ ኮሚቴው ፡-
1.በቀበሌው ነዋሪዎች ይዞታ ሥር የሚገኘውን መሬት ምዝገባ የሚያካሂዱ እያንዳንዳቸው 3 አባላት የሚኖራቸው እንደአስፈላጊነቱ ብዛታቸው በአካባቢው የሚወሰን ንዑሳን ኮሚቴዎች ያቋቁማል።።
2.ሥራውን አስተባብረው የሚሰሩ አንድ ሊቀመንበርና አንድ ፀሐፊ ይኖሩታል።።
3.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው በምርጫው ወቅት በአጣቃላይ ከሚመረጡት የኮሚቴው አባላት መካከል በእያንዳንዱ ንዑሳን ኮሚቴዎች ከአንድ ያላነሱ አባላት ማንበብና መፃፍ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል።።

15. የቤተሰብ ብዛት አጣሪ ኮሚቴ ስለማዋቀር

በእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ ክልል ውስጥ ከ 6 እስከ 9 አባላት የሚኖሩት በነዋሪው ህዝብ የሚመረጥ የቤተሰብ ብዛት አጣሪ ኮሚቴ ይቋቋማል።።
በተጨማሪም ኮሚቴው
1.በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ድንጋጌ መሠረት መሬት የመያዝ መብት የተሰጣቸውን የቀበሌ ነዋሪዎች ምዝገባ የሚካሄዱ እያንዳንዳቸው 3 አባላት የሚኖራቸው ሁለት ወይም ሦስት ንዑሳን ኮሚቴዎች ያቋቁማል
2.ሥራውን አስተባብረው የሚሰሩ አንድ ሊቀመንበርና አንድ ፀሐፊ ይኖሩታል
3.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው በምርጫው ወቅት በአጠቃላይ ከሚመረጡት የኮሚቴው አባላት መካከል ከ 3 ያላነሱት አባላት ማንበብና መፃፍ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል።።

16. በአጣሪ ኮሚቴዎች በአባልነት ለመመረጥ አስፈላጊ የሆኑ መመዘኛዎች

በኮሚቴዎቹ አባልነት ለመመረጥ ነዋሪዎች የሚከተሉትን መመዘኛዎች የሚያሟሉ መሆን ይኖርባቸዋል።።

localities stated under the provision of article10 and 11 of this proclamation.

## PART FOUR
## Committees to be established for the implementation of the Proclamation.

13. **The establishment of land possession and family size verifying, and allotting committee**

For the implementation of this proclamation in the locality of each rural keble family size and land possession verifying, and allotting committees shall be established.

14. **Organization of land possession verifying committee**

In the locality of each rural kebele land possession verifying committee, nominated by the in habitants shall be established; in addition the committee shall:
1. Establish sub committees, each consisting of three members and whose numbers to be decided by the concerned locality as may be necessary to carry out the act of registering the land under the possession of the in habitants of the kebele.
2. Have one chairman and secretary who co - ordinate and perform the activities.
3. With out prejudice to the details provided in sub article 1 and 2 of this article,in each sub committees there shall be elected not lass than one nember who can read and write amongst all members nominated in the period of the election.

15. **Organizing family size verifying committee**

In the locality of each rural kebele there shall be established family size verifying committee consisting of 6-9 members nominated by the inhabitants. In addition the committee shall:
1.Establish two or three sub committee each consisting of 3 members that carry out the registration of the in habitants of the kebeles who have got the right to hold a land persuant to the provision of article11. of this proclamation
2. Have one chairman and a secretary who co-ordinate and perform the activities.
3. With out prejudice to the details provided in sub article 1 and 2 of this article there shall be not less than 3 members 5 who can read and write, amongst all members of the committee nominated in the period of the election

16. **The necessary criterias to be nominated as a member of the verifying committees**

The inhabitants in order to be nominated as a members of the committee should fulfil the following criterias
1. Have been living in the respective Kebeles for

1.በቀበሌው ከ5 ዓመታትና ከዚያ በላይ የኖሩ፣
2.በታማኝነታቸውና በመልካም ስነምግባራቸው የተመሰከረላቸው፣
3.ከአድሏዊነት፣ ከቦዘኔነትና ከወንጀል ድርጊት የፀዱ፣

17.<u>የአጣሪ ኮሚቴው ስልጣንና ተግባር</u>

ኮሚቴው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 እና 6 ድንጋጌ ሥር የተዘረዘሩትን ተግባራት ያከናውናል በተጨማሪም፣
1.በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት የቤተሰብ ብዛትን፣ የመሬት ይዞታን እና መሬት በይዞታ እንዲይዙ የተፈቀደላቸውን ነዋሪዎች ይመዘግባል፡፡
2.የተጠቀሰውን የምዝገባ ተግባር ሲያከናውን ከማንኛውም የቀበሌ ነዋሪ እና ከቀበሌው ጽ/ቤት ማናቸውም አስፈላጊ መረጃ እንዲቀርብለት መጠየቅ ይችላል፡፡

18. <u>የመሬት ይዞታ ደልዳይ ኮሚቴ አወቃቀር</u>

በእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ ክልል ውስጥ በነዋሪው ሕዝብ የሚመረጥ፣ ተጠሪነቱ ለመረጠው ሕዝብና ለቀበሌው መስተዳድር የሆነ ከ 10 እስከ 13 አባላት የሚኖሩት የመሬት ይዞታ ደልዳይ ኮሚቴ ይቋቋማል፣ በተጨማሪም ኮሚቴው፣

1.እንደአስፈላጊነቱ ከ 3 እስከ 5 የሚደርስ አባላትን የሚይዙ ሁለት ወይም ሦስት ንዑሳን ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል፣
2.አንድ ሊቀመንበርና ፀሐፊ ይኖሩታል፡፡

<u>19.በመሬት ይዞታ ደልዳይ ኮሚቴ አባልነት ለመመረጥ አስፈላጊ የሆኑ መመዘኛዎች፣</u>

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 16 ሥር የተደነገጉትና ለአጣሪ ኮሚቴዎች አባልነት የሚያበቁ መመዘኛዎች፣በተመሣሣይ በደልዳይ ኮሚቴ አባላት ምርጫ ላይ በመመዘኛነት ያገለግላሉ፡፡

20.<u>የደልዳይ ኮሚቴው ስልጣንና ተግባር</u>

1.ኮሚቴው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 መሠረት የተዘረዘሩትን ተግባራት ያከናውናል፣
2.መሬት በሚያከፋፍልበት ወቅት የድልድሉን ተግባር በሙሉ ኃላፊነት ያከናውናል፡፡

21.<u>በደልዳይ ኮሚቴው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ስለማቅረብ፣</u>

1. በእጣ አወጣጥና ድልድል ተግባር ላይ በደል ተፈጽሞብኛል የሚል ማንኛውም የቀበሌው ነዋሪ፣ ኮሚቴው የድልድል ተግባሩን ባጠናቀቀ በ3 ቀን ጊዜ ውስጥ አቤቱታውን ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል፣

2. በደልዳይ ኮሚቴው ውሳኔ ቅር የተሰኘና አቤቱታውን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1ሥር

five years and above.
2. Have good reputation for honesty and moral standing.
3. Free from undue partiality, lumpen and crime.

17. **<u>Power and duty of the verifying committee</u>**

The committee shall perform the activities enumerated in the provision of article 5 and 6 of this proclamation. And in addition:
1. Shall register the family size the land in possession and the inhabitants allowed to hold land persuant to sub article 1 of article 14 and 15.

2. It may require while carrying out the activities of registration, the inhabitants and the offices of the respective kebele, any necessary evidence to be submitted to it.

18. **<u>The organization of the allotting committee</u>**

In the locality of each rural kebele a land possession allotting committee shall be established consisting of 10 -13 members to be nominated by the inhabitants and accountable to the public that elected it and to the kebele administration . In addition the committee shall:

1. Establish 2 or 3 sub committees consisting of 3 - 5 members as may be necessary.
2. Have one chairman and a secretary.

19. **<u>The necessary criterias to be nominated as members of the allotting committee</u>**

The criterias set for nominating members of the verifying committee provided under article 16 of this proclamation shall apply mutatis mutandis for nominating members of the allotting committee.

20. **<u>The power and duties of the allotting committee</u>**:
1. The committee shall: Perform the duties stipulated under article 7 of this proclamation.
2. Perform while distributing land the allotting activities with complete responsibility.

21. **<u>Apealing against the decision of the allotting committee</u>**

1. Any inhabitants of the respective kebele who claims that he is mistreated in the process of casting a lot and allotting activities may submit his petition to the grievance hearing committee with in the period of 3 days right after the committee has completed its allotting activities.
2. The petition of any inhabitants of the respective kebele who has been dissatisfied with the decision of

በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያላቀረበ የቀበሌ ነዋሪ አቤቱታው ተቀባይነት አይኖረውም።።

22.<u>የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ስለማቋቋም</u>

1.በደልዳይ ኮሚቴ የሥራ ሂደት ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ነዋሪ አቤቱታ የሚያቀርብበት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ይቋቋማል፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር በተደነገገው መሠረት የሚቋቋመው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ከደልዳይ ኮሚቴ ከሀገር ሽማግሌዎች እና ከቀበሌ ተመራጮች የተወጣጡ እና ከ5 እስከ 7 የሚደርሱ አባላትን የሚይዝ ይሆናል።።

23.<u>የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር</u>

የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1.በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 ድንጋጌ መሠረት የሚቀርቡለትን አቤቱታዎች መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፣
2.የመሬት ድልድሉ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ ሳምንት ባለው ጊዜ ውስጥ የሚቀርቡለትን ቅሬታዎች መርምሮ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፣
3.የሚሰጠው ውሳኔ ይግባኝ አይኖረውም፣
4.ውሣኔውን ለማስፈፀም እንደ አስፈላጊነቱ የአካባቢውን ሚሊሻ ወይም ፖሊስ ሊጠቀም ይችላል፣
5.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 2 ሥር በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተግባሩን ካጠናቀቀ በኃላ ይፈርሣል፣
6.በሥራ እንቅስቃሴው ወቅት በእጁ የተገኙ ሠነዶችን በሙሉ ለቀበሌው ጽ/ቤት ያስረክባል፣

<u>24. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ስለሚመለከታቸው ጉዳዩች፣</u>

በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሚታዩት በሽሚሽጉ ሂደት መሬት እንደያገኙ የተፈቀደላቸው አርሶ አደሮች የሚያነሷቸው ከዚህ በታች የተመለከቱትን ቅሬታዎች ብቻ ይሆናል።።

1.የመሬት ይዞታ መመጣጠን
2.የለም መሬቶች ሚዛናዊ ክፍፍልን፣
3.የእጣ አወጣጥን

<u>25. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት</u>

ከቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት መካከል ሁለት ሶስተኛው በስብሰባው ከተገኘ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፣
በተጨማሪም ኮሚቴው፣

1.የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች በቃለ ጉባዔ ይይዛል፣
2.ውሣኔዎቹም በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፣

the allotting committee, shall not be acceptable un less submitted in the time limit provided under sub article 1 of this article.

22. **<u>Organizing the Grievance hearing committee</u>**
1. Theire shall be established a grievance hearing committee, where any inhabitant who has complaints in the process of the activities of the allotting committee, may submit his/ her petition too.
2. The grievance hearing committee which is to be established persuant to the provision of subarticle 1 of this article, shall have 5 - 7 members, consisting from the allotting committee, elder inhabitants and kebele elects.

23. **<u>The power and duties of the Grievance hearing committee</u>**
The grievance heaving committee shall have the following powers and duties:

1. Render final decision, by examining the petition submitted to it, persuant to the provision of article 21 of this proclamation.
2. Render it's decision with in a period of a week, up on complaints submitted to it, after the allotting activities have been completed.
3. No ppeal shall be lodged upon its final decision.
4. May use the local militia or police, as may be necessary, in order to enforce its decision.

5. Shall dissolve, with in the period specified in sub article 2 of this article after completing its activities.
6. shall hand over, all the documents to the kebele office, which had been in its hands while performing its activities.

24. **<u>Matters to be entertained by the grievance hearing committee</u>**

Matters to be entertained by the grierance hearing committee shall be, only of the following complaints raised by the peasants who are allowed to hold land in the process of reallotment.

1. Apportionment of land possession
2. Fair distribution of fertile lands.
3. Casting a lot.

25. **<u>Meeting procedures of the grievance hearing committee</u>**
There shall be a qourum where the two third of the members of the grievance hearing committee are present at it's meeting. In addition the committee shall:

1. Hold a minute for decisions it render.
2. Pass its decisions by a majority vote.

26. ቃለ መሀላ ስለመፈፀም

አዋጅን ለማስፈፀም የሚቋቋሙ የመሬት ይዞታና የቤተሰብ ብዛት አጣሪ፣ የመሬት ይዞታ ደልዳይና የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ሥራ ከመጀመራቸው በፊት በህዝብ ፊት ቃለ መሀላ ይፈጽማሉ።

27.የይዞታ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት

በእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ ክልል፣ የመሬት ድልድሉ ከተጠናቀቀ በኃላ የቀበሌው መስተዳድር ለእያንዳንዱ አደስ የገጠር መሬት ባለይዞታ የመሬት ባለይዞታነት ሕጋዊ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት ይኖርበታል።

ክፍል አምስት
ልዩልዩ ድንጋጌዎች

28. ክስን ስለማገድ

1. በዚህ አዋጅ ድንጋጌ መሠረት በየቀበሌው በሚቋቋሙት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የሚወሰኑ ውሣኔዎችን ወይም የሚወሰዱ እርምጃዎችን ሕጋዊነት በመቃወም፣ ማንኛውንም ክስ ወይም ይግባኝ ለቀበሌ ፍትህ ኮሚቴ ወይም ለመደበኛ ፍ/ቤቶች ማቅረብ አይፈቀድም፣
2. ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ የመሬት ሽግሽጉ በሚካሄድባቸው ቦታዎች በቀበሌ ፍትህ ኮሚቴ ወይም በመደበኛ ፍ/ቤቶች የተያዙ የገጠር መሬት ይዞታን የተመለከቱ ክርክሮች በሙሉ ተሰርዘዋል።
3.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመሬት ሽግሽጉ በሚካሄድባቸው የገጠር አካባቢዎች በፍትህ ኮሚቴዎች ወይም በመደበኛ ፍ/ቤቶች የተያዙ ነባር የመሬት ይዞታ ክርክሮችን በተመለከተ፣ ደልዳይ ኮሚቴው ተገቢውን ማጣራት እያደረገ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጥባቸዋል።

29.የመስተዳድር አካላት ኃላፊነት

በየደረጃው የሚገኙ የመስተዳድር አካላት፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል።
1.የመሬት ሽግሽጉን የመምራት፣
2.ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በየቀበሌው ለሚቋቋሙት የተለያዩ ኮሚቴዎች የማቴሪያልና የፋይናንስ እገዛ የማድረግ፣

30. የቀበሌ መስተዳድር ኃላፊነት

እያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ መስተዳድር ይህንን አዋጅ የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት።

31. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያለው ግለሰብ፣ ግላዊና መንግሥታዊ የሆኑ ድርጅቶች ይህን አዋጅ በማስፈፀም ረገድ የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

26. **Execution of an oath**

The land possession and family size verifying committee, and the land allotting and grievance hearing committee established for the implementation of this proclamation shall execute an oath before the public prior to the assuming of their duties.

27. **Issuance of holding certificate**

After the completion of reallotment of land in each locality of the rural kebele, the kebele administration shall issue a title document to each new land possessers evidencing his legal possession of land.

**PART FIVE**
**MISCELLANEOUS PROVISIONS**

28. **Prohibition of court action**

1. No suit or appeal might be brought to the justice committee of the kebele or ordinary courts of law, challenging the legality of any decision passed or action taken by the grievance hearing committee, established in each respective kebele.

2. As of the effective date of this proclamation, in the places where the reallotment of land is to be carried, all cases involving rural land possession pending in the justice committee of the kebele or ordinary courts of law are hear by annulled.
3. With out prejudice to the provision of sub article 1 and 2 of this article, the allotting committee, after the appropriate verification, shall render its final decision upon former cases involving land possession pending in the justice committee or ordinary courts of those rural localities, where the reallotment of land is to be carried.

29. **Responsibility of the administrative organs**

The administrative organs on every level shall have the following responsibilities to:

1. Direct the reallotment of land
2. Render material and financial support to various committees to be established for the implementation of this proclamation in each respective kebele.

30. **The responsibility of the kebele administration**

Every rural kebele administration shall have the responsibility to execute this proclamation.

31. **Duty to co - operate**

Any concerned individual, private and governmental organizations are duty bound to cooperate for the implementation of this proclamation

32. ስለቅጣት

ይህ አዋጅ በሥራ ላይ እንዳይውል ያሰናከለ ወይም ለማሰናከል የሞከረ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ይቀጣል፡፡

33. ከሌሎች ሕጉች ጋር ስላለው ቅራኔ

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

34. ደንብ የማውጣት ስልጣን

የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይህንን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያግዙ ተጨማሪ ደንቦችና መመሪያዎች ማውጣት ይችላል፡፡

35.አዋጅ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህርዳር
ጥቅምት 27 ቀን 1989 ዓ.ም.
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ምክር ቤት

32. **Penalty**

Any individual who obstructs the execution this proclamation or attempts to commit the same, shall be penished persuant to the appropriate provision of the penal code.

33. **Conflict with other laws.**

Any law inconsistent with this proclamation shall not apply in respect of matters provided for in here.

34. **Power to issue regulation**

The executive committee of the region may issue additional regulations and directives for the purpose of the implementation of this proclamation.

35. **Effective date**

This proclamation shall enter in to force on the date of its ratification by the council of the Amhara National Regional State.

**Done at Bahir Dar**
**This 5th day of November, 1996.**
**Council of the Amhara National Regional State.**

15